**Barn som upplever våld i en nära relation - Amhariska**

# በቅርብ ዝምድና መሓል ለነውጥ የሚዳረግ ልጅ

አንድ ልጅ ለሚከተሉት ሁኔታዎች ሲዳረግ፥ ነውጥ ተፈጸመበት ማለት ነው።

- ለነውጥ መጋለጥ (ከምት፥ ግፍትሪያ፥ ግብረ ሥጋዊ መደፈር፥ መዋረድ እስከ ስነልቦናዊ ድሽቀት)
- ነውጥ ሲተገበር ማየት ወይም መስማት፥
- የነውጥ ምልክቶችን ማየት (ለምሳሌ ገላ ላይ ሰማያዊ ምልክት፥ የተሰባበሩ ዕቃዎች፥ ፍርኀት)
- ቤት ውስጥ ያለው የጭንቀት ድባብ ሲሰማው።

ኣሳዳጊዎች ባይመስላቸው፥ አብዛኛዎቹ ልጆች ቤተሰብ ውስጥ የሚካሔደውን ነገር በደንብ ይገነዘባሉ። ልጆች የውስጥ ስሜታቸውን ኣይገልጹም እንጂ ያቀረቡት ሰው ሲከፋው ይታወቃቸዋል። በመካያው ልጆች ሲከፋቸው ወይም ሲጨነቁ በሚጫወቱበት ጊዜ ወይም በባኅሪያቸው ላይ በሚታይ ለውጥ ያስታውቃሉ።

## የኣሳስቦኛል ማመልከቻ ያስገቡ

አንድ ልጅ ያልተመቸው መስሎ ከታዮት፥ ለማህበራዊ ጉዳይ ጽ/ቤት የአሳስቦኛል ማመልከቻ ያስገቡ። ለማህበራዊ ጉዳይ ጽ/ቤት ጉዳዩን መርምሮ ውይይታዊ ድጋፍ ከመስጠት ኣልፎ አስፈላጊውን እርምጃ ይወስዳል።

አንዳንድ የሙያ ተቋሞች የአሳስቦኛል ማመልከቻ የማስገባት ሕጋዊ ግዴታ ኣለባቸው። ይህ ለምሳሌ ያህል ት/ቤትን፥ የጤና ተቋማትንና ፖሊስን ይመለከታል።

## ለነውጥ የሚዳረግ ልጅ ድጋፍ

ልጁና ኣሳዳጊዎቹ ከማህበራዊ ጉዳይ ጽ/ቤት ድጋፍ ማግኘት ይችላሉ። ለምሳሌ

- ውይይታዊ ድጋፍ
- የልጆች ቡድን ውስጥ መሳተፍ
- የወላጅ ሚናን አስመልክቶ ለልጁ ሲባል የሚደረግ ድጋፍ
- አንድ የሚገናኙት ሰው ወይም ቤተሰብ
- ጉዳዩ አስቸኳይ ከሆነ ሌላ እርምጃ፥ ለምሳሌ ግዚያዊ መቆያ ቤት።

ለአስቸኳይ ጊዜ ሁሌም 112 ይደውሉ።

## ከእነዚህ ጋር ግንኙነት ያድርጉ፥

- **ሥራው/ኀላፊነቱ:** Socialtjänst Vårgårda
- **ስልክ ቁጥር:** Telefon växel 0322-600 617
- **ድረገጽ:** www.vargarda.se
- **ኣድራሻ:** Kungsgatan 45